# ምዕራፍ አራት

## ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ)

### ማድነቅ

ስነ-ውበት ጥበብ ነው፡፡ ይህም ጥበብ በርካታ ሙያዎችን በማካተት ጠለቅ ያለ እውቀትንና ማስተዋልን የሚፈልግ የሰው ልጅ የአዕምሮ ውጤት ነው፡፡ በዚህም በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በትያትርና በዕይታ ጥበብ አማካኝነት የሚተላለፍ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የምናገኛቸውን ጥበባት ለሃገራችን ያላቸውን ዋጋ መረዳት እንድንችል በዚህ መዕራፍ እንመለከታለን፡፡

ኢትዮጵያዊ የሆኑ ልናውቃቸውና ልናደንቃቸው ከሚገቡ ሥነ-ውበታዊ እሴቶቻችን እንደ ተረቶች፡ የአምልኮ ዝማሬዎች ወይም ዜማ እና ኢትዮጵያዊ ስዕል፡ ቅኔ፡ እንጉርጉሮ፡ የሙሾ ግጥሞች፤ በክብረ በዓላት፣ በሰርግ፡ በልጆች ጨዋታ፡ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎቻችን እንዲሁም ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡ ወጎች፡ ቀልዶች፡ ፉከራ፡ ቀረርቶ፡ ሽለላ እና ግጥሞች ሌሎችም የክወናና ዕይታ ጥበባት ውጤቶች የሆኑ ስነ-ውበታዊ እሴቶቻችን ናቸው፡፡ እነዚህ የአገር በቀል እወቀቶች እሴቶቻችንን ስለሆኑ ልናደንቃቸውና እና ልናውቃቸው ይገባል፡፡

ተማሪዎች ሃገራቸውን የበለጠ ይወዱና ያከብሩ ዘንድ እንዲሁም የበኩላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ሃገር ገንቢ ዜማዎችን በትምህርት ውስጥ ማካተት ተገቢ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

### አጥጋቢ የመማር ውጤት

- የአገራዊ ጥባባትን (በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሙዚቃ ጥበባትን) በዝማሬ ያደንቃሉ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ያቀርባሉ፡፡
- ስነ-ውበታዊ እሴቶችን ያውቃሉ፡፡
- ባህላዊ የክወናና የእይታ ጥበባትን  ይረዳሉ፡፡

ኢትዮጵያ ሃገራችን የብዙ ባህል ባለቤት ነች፡፡ እነዚህም የተለያዩ ባህሎቻችን ከህዝቦች ጋር ለብዙ ዘመናት አብረው የቆዩ ናቸው፡፡ እነዚህን የባህል ክዋኔዎችንና የጥበብ ስራዎችን አስቀድሞ በማየት፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በሌሎች ስሜት ህዋሳቶቻችን በመጠቀም መገንዘብና ማድነቅ ተገቢ ነው፡፡ በተገቢው ሁኔታ ለማድነቅ ፍላጎትና ተነሳሽነት መኖርአስፈላጊ ነው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቁ ዝርዝር ውጤቶች፡-

- የኢትዮጵያን ሙዚቃ ያደንቃሉ፡፡
- ኢትዮጵያን ሙዚቃ ለምን እንደሚያደንቁ ያውቃሉ፡፡
- ሀገራቸውን በዝማሬ ይገልፃሉ፡፡

## 4.1 የኢትየጵያ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ

- ኢትዮጵያ እንዳሏት ብሄር ቤረሰቦች ብዛት፤ ባህላዊ ክወና ጥበቧም እንደዚሁ አጅግ በርካታ ነው፡፡ እነዚህም ባህሎች ብርቅና ድንቅ መሆናቸውን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህም ባህሎቿ ሙዚቃ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

- ከዚህ አንጻር ተማሪዎች በአካባቢያችሁ እንዲሁም በመገናኛ ብዙኋን የሚያውቋቸውን የባህል ሙዚቃዎች በደንብ በማዳመጥ እንዲመረምሩ ያስፈልጋል፡፡
- የኢትዮጵያ ባህላዊ ክዋኔዎች ሃይማኖታዊ ይዘት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል፡፡
- የሃገራችንን የባህል ሙዚቃ ከምናደንቅባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሚከተሉትን መጥቀስ እንችላለን፡፡

### 4.1.1 ለብዙ ዘመናት ከውጭ ሀገር ተፅእኖ ስር ያልወደቀ መሆኑ

በርካታ የአለማችን ሃገራት በአውሮፓውያን ቅኝ በመገዛታቸው ምክንያት የሙዚቃ ባህላቸውም ሆነ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸው አውሮፓውያንን ባህሪ የያዘ ነው፡፡

ኢትዮጵያውን ግን በጀግኖች አባቶቻችን ደምና አጥንት ዳር ድንበሯን በማስከበራቸውና ቅኝ ገዢዎችን አሳፍረው በመመለሳቸው የውጭ ተፅእኖ ሙሉ በሙሉ ሊያርፍብን አልቻለም፡፡

- የአባቶቻችንን ተጋድሎ በአቅማቸው እንዲረዱ አጭር ታሪክ ይንገሯቸው፡፡

### 4.1.2 በተለያዩ አካባቢ ብዙ አይነት የሙዚቃ ባህል መኖራቸው፡-

በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በምእራብ እንዲሁም በመካከለኛው ኢትዮጵያ ያሉት የሙዚቃ ባህሎች በምት፣ በድምፅ አደራደር (ቅኝት)፣ በሙዚቃ መሳሪያ፣ በውዝዋዜ፣ በአለባበስ…ወዘተ አንድነትም ልዩነትም አላቸው፡፡

- ለምሳሌ ክራር በተለያየ አካባቢ የተለያየ አይነት አሰራርና ስያሜ አለው፡፡ በአማራ፣ በትግራይ፣ በጋምቤላ (ዱል)፣ በወላይታ (ዲታ)፣ በኮንሶ (ሃቼ) ሲባሉ የራሱ ሆነ አሰራርና ጥበብ አለው፡፡

### 4.1.3 በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች መኖራቸው፡-

ከዚህ በታች ተዘረዘሩት ሙዚቃ መሳሪያዎች በሌላ ሃገር ቢኖሩ

እንኳን በአሰራርና በአጨዋወት ኢተዮጵያውያን ለየት ይላሉ፡፡

- ማሲንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንት፣ ተለያዩ አይነት ከበሮዎች፣ እምቢልታ፣ ነጋሪት፣ ፅናፅል፣ በገና፣ ዲታ(የወላይታ ክራር)፣ መለከት፣… ወዘተ

መልመጃ 1፡- ክራር፣ ማሲንቆና ሌሎችንም የሙዚቃ ባህላዊ መሳሪያዎች በስዕል፣ በቪዲዮ፣ በፎቶ …ወዘተ እንዲመለከቱና አይተው እንዲለዩ እንዲሁም እንዲገነዘቡ ያግዟቸው፡፡

### 4.1.4 ለተለያዩ አላማዎች መዜማቸው

- ለሃማኖታዊ ክብረ በአላት የሚዜሙ ዜማዎች
- ለባህላዊ ክብረ በአላት የሚዜሙ ዜማዎች
- ለደስታ፣ ለሃዘን፣ ለጦርነት፣ ለፍቅር፣ ለህፃናት የሚዜሙ ዜማዎች

### 4.1.5 ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስርና ቁርኝት ያለው መሆኑ

ሙዚቃ ከኢትዮጵያውያን ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ለዚህም ማስረጃነት ማንኛውም ክንውናችን ከሙዚቃ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ የትኛውም  አይነት ድግስ ቢኖር፣ ልደት፣ ሰርግ፣ ግብዣ፣ ክብረ በአል፣ ጦርነት፣ ሃዘን፣ የጋራ ስራ ቢኖር፣ ልጆች ቢሰበሰቡ፣ መንፈሳዊ ጉዳዮች ቢኖረን …ወዘተ ከሙዚቃ ውጭ የማይታሰቡ ናቸው፡፡

መልመጃ 2፡- በአካቢያቸው ሚያውቁትን ማንኛውንም ዜማ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡

### 4.1.6 ለሃገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገሮች እንደመለያ አርማ የሚያገለግል መሆኑ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአለም ላይ ከምትታወቅበት ነገር አንዱ የባህል ሙዚቃና ውዝዋዜ ናቸው፡ ፡ በመሆኑም ሙዚቃ ስልተ-ምት፣ ውዝዋዜው፣ አልባሳቱ በአንድ ላይ ኢትዮጵያዊነት መለያን ያጎናፅፋሉ፡፡

በመሆኑም አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ እነዚህን የሙዚቃ ስልተ-ምት በማዳመጥና ውዝዋዜውንና አልባሳቱን በማየት ኢትዮጵያዊ መሆናችንን ይለያሉ ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሀገር ሙዚቃ፣ አልባሳት ወዘተ የምንለይበትን ተማሪዎች እንዲጠቅሱ ያድርጉ፡፡

መልመጃ 3፡- ቀጥሎ የተቀመጡትን ኖታና ግጥሞች በማጣመር አዘምሯቸው፡፡

የሚቀጥለው የዜማ ግጥም ሃገርን ከወራሪዎች ለመታደግ ከሚቀርቡ ስንኞች ውሰጥ የተወሰኑትን እንደምሳሌ ማየት እንችላለን፡፡

ኢትዮጵያዊ ጀግና
የማይበገረው፤
እንኳን ለሀገሩ ይተርፋል ለሌላው፡፡
ስጋዬንም ብሉ
አጥንቴንም እንኩ፤
ነገር ግን ሃገሬን አትዮጵያን አትንኩ፡፡

መልመጃ 4፡- ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የታዳጊ ልጆች ዜማ ግጥሙን እያነበቡ እንዲዘምሩ አድርጉ፡፡ ከማዜማቸው በፊት ሙዚቃውን እንዲያዳምጡ ይርዷቸው፡፡

የዜማና የግጥም ርዕስ፡- እምዬ ኢትዮጵያ (ከኢትዮጵያ ልጆች የተወሰደ)

እናቴ ኢትዮጵያ ክብርና ኩራቴ

እድለኛነት ነው ባነቺ መጠራቴ፡፡

የሊቃውንት ምድር

ባለብዙ ሚስጥር፡፡

የሰው ልጅ መገኛ


ኢ ትዮ ጵያ ዊ ጆ ግ ና
ሰ ጋ ዬ ን ም ብ ሉ
የ ማ ይ በ ገ ሬ ው
አ ጥን ቱ ንም አ ን ኩ
እ ንኪን ለ ሀ ገ ሩ
ነ ጂ ግ ን ኢ ት
ይ ተ ርፋል ለ ሌ ላ ው
ዮ ጵ ያ ን እ ትን ኩ



በእምነት መዳኛ፡፡

እናቴ ኢትዮጵያ ክብርና ኩራቴ

እድለኛነት ነው ባነቺ መጠራቴ፡፡

ከጥንት መሰረትሽ

በቅኝ ያልተገዛሽ

በታሪክ ባህልሽ

አብዝተሽ የታደልሽ

በመዝሙር በዜማ

ብክሩናን ያገኘሽ

በፊደል በቁጥር

መለያ የተሰጠሽ፡፡

እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ክብሬ ነሽ

እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ክብሬ ነሽ፡፡

መልመጃ 5፡- የሚከተለውን ግጥም ዜማውን በማዳመጥ በዜማው ያዚሙ፡፡ በዚህ ዜማ ውስጥ ከመዝፈን ባሻገር ስለኢትዮጵያ በጥልቀት እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡

ግጥምና የዜማ ርዕስ፡- አንድ ኢትዮጵያ (እጅጋየሁ ሽባባው)

የማንነቴ መለኪያ
ኩራቴ መመኪያዬ ክብሬ፤
የሶስት ሺ አመት እመቤት
አንድ ናት ሀገሬ፡፡
እቴ አንቺ የኔ ሙሽራ
ሀገሬ እስኪ ልጠይቅሽ፤
ያገቡሻል ይፈቱሻል
ያጨሻል አሁንም ድንግል ነሽ፡፡
ከክብርሽ በታች ወደቁ
ነገስታት በፍቅርሽ ተነድፈው፤
ደናግላን መነኑልሽ
አለምን ደስታቸውን ጥለው፡፡
እማማ እናት ኢትዮጵያ
እማማ አንቺ እናት አለም
እማማ እናት ኢትዮጵያ
እማማ አንቺ እናት አለም፡፡........

የመማር ማስተማር ስልት፡-

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ (ዘምሮ) ማሳየት
- ማሳተፍ
- የሚያውቁትን በመጠየቅ ከዚያ መነሳት

የመማሪያና ማስተማሪያ መርጅያ መሳሪያ ፦

- የመማሪያ ክፍል
- ጥቁር ወይም ነጭ ሰሌዳ ከነመፃፊያው
- ደብተርና፣ እስኪቢርቶ ወይም እርሳስ
- ቴፕ ሪኮርደር፣ ቪድዮ ማጫወቻ

መልመጃ 6፡- በአካባቢያቸው የሚያውቁትን ሃገራዊ ዜማ ለመምህራቸውእንዲያዜሙ ያበረታቷቸው፡፡

## 4.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ የውዝዋዜ ጥበባት

ውዝዋዜ የአንድ ማህበረሰብ ስነ-ውበታዊ መገለጫ ተደርገው ከሚወሰዱ ኪነ-ጥበባዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ ያላት ትልቅ እና የስልጣኔ መገለጫ ከሆኑ ቀደምት አገራት አንዷ ነች፡፡

ዝርዝር አጥጋቢ የማስተማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ ውዝዋዜን ያቀርባሉ፡፡
- የተለያዩ አይነት የውዝዋዜ ምንጮችን ያውቃሉ፡፡

ውዝዋዜ እንደ ፈለቀበትና እንደሚነገርበት አካባቢ ባህል የተለያዩ መልኮች አሉት፡፡ ባንድ ቋንቋና ባህልም እንኳን ቢሆን የተለያዩ የውዝዋዜ ስልቶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ወላይትኛ፣ ጉራጊኛ፣ ጎጃምኛ፣ ጎንደርኛ ወዘተ------፡፡

ውዝዋዜ እንደ የባህሉ አይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ፡ ከሙሾ ወይም ከሰርግ ጭፈራ ጋር አንድ አይደለም፡፡ ቀረርቶ የሚያሰማው ሰው ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ እና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ አይኑን እያጉረጠረጠ፣ ጦር እሰበቀ ጋሻ አመካከትን እያሳየ ነው የሚከው ነው፡፡ ስለዚህ ውዝዋዜ በሀዘንም በደስታም ማህበረሰቡ ስሜቱን የሚገልጽበት፣ የሚዝናናበት፣ የሚደሰትበትና የሚጽናናበት አንዱ የክዋኔ ጥበብ ነው፡፡

## መልመጃ 1

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።</u>

1. ባህላዊ ውዝዋዜ አንድ ማህበረሰብ ስሜቱን የሚገልጽበት የክዋኔ ጥበብ ነው። እውነት

2. ባህላዊ ውዝዋዜ ከቦታ ቦታ የተለየ መልክ እና እንቅስቃሴ ሊኖረው ይችላል። እውነት

3. የቀረርቶ እና የፉከራ ክዋኔ ከሰርግ ጭፈራ ጋር አንድ ነው። እውነት

የማስተማርያ ስልቶች፦

- ገለጻ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- በቪዲዮ እና በስዕል ማሳየት
- እንዲለማመዱ ማድረግ

የማስተማሪያ መሳሪያዎች

- የመማሪያ ክፍል
- የምስልና የድምፅ ማጫዋቻ
- ፎቶ ግራፍ(ስዕል)
- የምስልና የድምፅ ግብዓቶች

## 4.3 የኢትዮጵያ ባህላዊ የትያትር ጥበብ

በኢትዮጵያ አገራችን ባህላዊ የሆኑ ኪነ-ጥበባዊ መገለጫዎች አሉ። በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች፣ በየወቅቱና በየዘመናቱ የሚወሩት ተረቶች፣ በአምልኮ ስርዓቶች ላይ የሚደረደሩት ውዳሴ አማልክትና ዝማሬዎች አሉ። እንዲሁም በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ በሌሎችም መሰል ስራዎች ላይ የሚዜሙና የሚነገሩ ኪነ-ጥበባዊ መገለጫ ያላቸው ክንዋኔዎች ይካሄዳሉ።

በከበት ስምሪት ጊዜ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች በቀብር ስነ-ስርዓትና ሀዘን ላይ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች፣ በክብረ-በዓላት፣ በሰርግ፣ በልጆች ጨዋታ ላይ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎችም ይገኛሉ።

በደቦ፣ በእድር፣ በእቁብና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ላይ የሚሰነዘሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ የሚነገሩ ወጎችና ቀልዶችም መጠቀስ ይቻላል። ስለጀግኖች እና ተደናቂ ግለሰቦች የተነገሩ እና የተፃፉ ግጥሞችና አፈታሪኮች እንዲሁም ሌሎችም በክወና ጥበባት የሚቀርቡ አሉ።

የተለያዩ ማህበረሰቦች ስለራሳቸው፣ ስለሰው ልጅ፣ ስለአካባቢያቸውና ባህላቸው እንዲሁም በአጠቃላይ ስለ ሀገር ያላቸውን አመለካከቶች ከላይ በተጠቀሱት ጥበባት ያቀርባሉ።

መልመጃ 1፡- ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ድራማዊ ይዘት ያላቸው ጨዋታዎችን በማስመሰልና ድምፅ በማሰማት ለጎደኞቻቸው ሰፋ ባለ ክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎቹን እንዲያሳዩ ማድረግ።

- የቤት እንስሳዎችን፡ የዱር አውሬዎች የአውሬዎች ድምፅ፤
- መኪና ወይም ብስክሌት መንዳት፤
- ፈረስ ወይም በቅሎ መጋለብ፤
- ልብስ መልበስና እና ማውለቅ፤
- ደስታንና ቅሬታን መግለፅ፤
- እንደአሞራ መብረር እንደ ውሃና እሳት እንቅስቃሴዎችን ማሳየት፡

መልመጃ 2፡- ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ድራማ በአራት አራት በማድረግ የተፃፈው ቃለ-ተውኔትን በመበታተን ለልጆች ሚና ሚና በመስጠት የአባት፣ የእህት፣ እናትና ሌባው ልጅ አድርጎ እንዲሰሩ ማገዝ ካጠኑትም በኋላ ተራ በተራ እንዲያቀርቡ ማድረግ።

### 4.3.1 እኔ ነኝ ውሮ

አንድ በገጠር ውስጥ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር የ14 ዓመት ልጅ ማታ ማታ መብራት ሲጠፋ ከተኛበት እየተነሳ እናቱ ያስቀመጡትን ወተት እየሰረቀ ይጠጣል። እናትም ሌባው ልጃቸው መሆኑን ቢረዱትም ቢናገሩ አባቱ ይገድለዋል ብለው ስለሚሰጉ ዛሬም ወተቱን ድመቷ ጠጥታው አደረች እያሉ በደላቸውን ለቤተሰብ ያሰማሉ።

አንድ ቀን ሌሊት እንደተለመደው ይሄ ልጅ ሁሉም ተኝቷል ብሎ በገመተበት ሰዓት ተነስቶ ሲያንጎዳጉድ

አባት ይነቁና፡ ማን ነው? ይላሉ።

ልጁም ድመት ለመምሰል ሚያው--- ይላል።

አባት ከራስጌያቸው ያለውን ባትሪ ሊያበሩ ሰበብ የተፈጠረባት ድመት ከግርጌ መተኛቷን ያረጋግጣሉ። ያለጥርጥር ጓዳውን የሚያንጎዳጉደው ሰው መሆኑን የተረዱት አባት ከመኝታቸው ተነስተው ወደልጁ እያበሩ

ማን ነህ አንተ-- ሲሉ በቁጣ ጠየቁ፡፡

ተጋለጥኩኝ ብሎ የሰጋው ልጅም መጀመሪያ ድመቷን ለመምሰል ሚያው--- ካለ በኃላ እኔ ውሮ ነኝ... ሲል መልስ ሰጠ፡፡

በዚህ አባት፡ እናት እና የሌባው ልጃቸው ታላቅ እህት ተነስተው ጨለማን ተገን እያደረገ ወተት ሲደፉ የኖረውን ሌባ ያዙ፡፡ ወዲያው ምን እናድርገው.. ሲሉ መከሩ፡፡ አባት ሙልጭ አድርጌ ልግረፈው ሲሉ እህት ተስማማች፡፡ እናት ግን መግረፍ ሌብነቱን ቢያብሰው እንጂ ስለማያስቀረው ሌላ መፍትሄ ይፈለግለት አሉ፡፡ ቀጠል አደረጉና ዳግመኛ ወተት በዞረበት እንዳይዞር ከተፈለገ ሰሞኑን ያጠራቀምኩት ወተት ስላለ አንድ ግራሬ ሙሉ በግድ ይጋት፡፡ በጠጣው ወተት ላ ሌላ ወተት እንዲጠጣ መገደዱ ትልቅ ቅጣት ነው በማለት አስረዱ፡፡ በሃሳቡም ሁሉም ተስማሙና ልጁ እንዳይታገላቸው ሁለት እጆቹ ከምሶሶ ጋር የፊጥኝ ታስረው በትልቁ ግራሬ የተሞላ ወተት ቀርቦ መጋት ሲጀምር ያልቃል፡፡

የመማር ማስተማር ስልቶች፦

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ ማስረዳት
- በግልና በቡድን እንዲለማመዱ መድረግ
- መነባንቦቹን በቃል እንዲያጠኑ(እንዲይዙ) ማድረግ

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- መለማመጃ ክፍል፡
- ፎቶ ግራፎች
- የምስል ማሳያ ግብዓቶች
- ጥቁር ወይም ነጭ ሰሌዳ
- ጠመኔ ወይም የነጭ ሰሌዳ መፃፍያ

## 4.4 የኢትዮጵያ ባህላዊ የዕይታ ጥበብ

በሀገራችን ብዙ ባህላዊ የእይታ ጥበባት ውጤቶች ይገኛሉ። እነዚህ የዕይታ ጥበባት ውስጥ የቀለም ቅብ፣ ቅርጻቅርጽ፣ ኪነ-ህንጻ ልዩ ልዩ እደጥበባት እንዲሁም ጌጣጌጦች በስፋት ይገኙበታል። በዚህም ምዕራፍ እነዚህ የእይታ ጥበባት በሚገባ እናውቃለን እንዲሁም እናደንቃለን።

## የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የኢትዮጵያን ባህላዊ የእይታ ጥበባትን ምንነት ያውቃሉ፡፡
- የተለያዩ ባህላዊ የእይታ ጥበባት አይነቶች ማለትም ቀለም ቅብ፣ ቅርፃቅርጽ፣ ኪነ-ህንጻ እና እደ ጥበባትን ያውቃሉ፡፡
- እነዚህን ባህላዊ የእይታ ጥበባት ማድነቅ ይችላሉ፡፡

በሀገራችን ብዛት ያላቸው የዕይታ ጥበባት ይገኛሉ፡፡ ከአራተኛው እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን የተሰሩትን የዕይታ ጥበባት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ የሚገኙት የዕይታ ጥበባት፥ ዘመናዊ የዕይታ ጥበብ በሃገራችን መሰራት ሳይጀምር በፊት በአብዛኛው በቤተ ክህነት አካባቢ ሲሰሩ የነበሩትን ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ስራዎች ነው ከእነዚህ የዕይታ ጥበባት ውስጥ ሰፊውን ስፍራ የሚይዙት ደግሞ ሐይማኖታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ናቸው፡፡ በሁለተኛው ክፍል የምናገኛቸው ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ የዕይታ ጥበባትን እንደ ሽመና፣ የሸክላ ስራ፣ የጌጣጌጥ ስራዎች ሲሰሩበት የነበረውን ነው፡፡ ወደ እነዚህ ባህላዊ የእይታ ጥበባት ለሀገራችን ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ የላቀ ነው፡፡

### 4.4.1 ቀለም ቅብ

የቀለም ቅብ ስራ በሃገራችን ከሚገኙ ቀደምት ባህላዊ የእይታ ጥበባት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ይህ የጥበብ አይነት ለረጅም ዘመናት በተለያዩ መንገዶች ሲሰራ የነበረ ነው፡፡ በዋነኛነት ይሰራ የነበረው ግን በቤተ ክህነት አካባቢ ሲሆን በውስጡ የሚይዘው ደግሞ ሃይማኖታዊ መልዕክቶችን የሚያንጸባርቁ የመጽሃፍ ቅዱስ ታሪኮችና ሌሎች ሃይማኖታዊ ገድሎችን በተጨማሪም የነገስታት ታሪኮች ላይ ያተኩራሉ፡፡ እነዚህን የቀለም ቅብ ስራዎች የሚሰሯቸው በየገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት ናቸው፡፡

እነዚህ የቀለም ቅብ ስራዎች ይሰሩ የነበሩት ስነ-ውበታዊ ጠቀሜታን ከመስጠት ይልቅ ሀይማኖታዊ አገልግሎትን ለመስጠት ታስበው ሲሆን የሚሰሩትን ስዕሎች ስንመለከትም አንድን መልዕክት ለተመልካቹ በቀጥታ ለማሳየት የተሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀለም ቅብ ስራዎች በውስጣቸው የተለያዩ ጽሁፎችንም ይይዙ ነበር፡፡

በኋለኛው ዘመን የተሰሩት የቀለም ቅብ ስራዎች ደግሞ ጭብጣቸውን ከመንፈሳዊ ታሪኮች ጎን ለጎን ዓለማዊ የሆኑትን የነገስታትን እና ቤተሰቦቻቸውን የእለት ተለት ክንዉኖች ፣ ታሪኮች፣ ገድሎች ላይ ያተኩሩ ነበሩ፡፡

ለምሳሌ፦

- የአድዋ የጦርነት ውሎን የሚያሳዩ ስዕሎች፣
- የአፄ ቴድሮስን ንግስና የሚያሳዩ ስዕሎች ይጠቀሱበታል፡፡

እነዚህ ባህላዊ የእይታ ጥበባትን ለማዘጋጀት የሚገለገሉባቸውን ግብዓቶች የሚያዘጋጁት በአከባቢያቸው በሚያገኟቸው የተፈጥሮ ውጤቶች ነው፡፡ ተፍቆ እና ተለስልሶ ተዘጋጀ የፍየል ቆዳ (ብራና) እና ለቀለማቱ ደግሞ ከአፈር፣ ከቅጠላቅጠል እና የተለያዩ የእንስሳት ተዋፅዖ ይጠቀሙ ነበር፡፡ እንዲሁም ሌሎች ማዋሃጃ እና ማጣበቂያዎችን በማዘጋጀት ይሰሯቸው ነበር፡፡

### 4.4.2 ኪነ-ሕንፃ

ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት እንደመሆኗ የተለያዩ ስልጣኔ የሚገልፁ የኪነ ሕንፃ ጥበባት ይገኙባታል፡፡ እነዚህ የኪነ ሕንፃ ጥበባት በብዛት የሀይማኖት ቦታዎች እና በቤተ መንግስታት ላይ እንመለከታቸዋለን፡፡ የሀይማኖት ስፍራዎች በብዛት አንድ ወጥ ድንጋይ በመፈልፈል ወይም ድንጋዮችን በመጥረብ ይሰሩ ነበር፡፡ በተጨማሪም በእንጨት እና በጭቃ የተሰሩ ባህላዊ እና ታሪካዊ የኪነ ሕንፃ ውጤቶች ይገኛሉ፡፡ በቤተ መንግስታት የምናየው የኪነ ሕንፃ ጥበብ ደግሞ ድንጋዮችን በመደርደር እና ተፈጥሯዊ የሆኑ የመለሰኛ መንገዶችን በመጠቀም ይሰሩ ነበር፡፡ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የኪነ ሕንፃ ጥበባት በሙሉ የተሰሩት ዘመናዊ የመስሪያ ማሽኖችን ሳይጠቀሙ በሰው ሃይል ብቻ ነው፡፡

### 4.4.3 የዕደ ጥበብ እና የጌጣጌጥ ስራዎች

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሄረሰቦች መኖሪያ እንዲሁም የብዝሃ ባህል መገኛ መሆኗ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ታሪክ እና ባሕል ያላቸው ብሄረሰቦች የባህላቸው መገለጫ የሆኑ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የዕደጥበብ ውጤቶችን እንዲሁም ትውፊቶቻቸውን የምናይባቸው የጌጣጌጥ ስራዎች አሏቸው፡፡ ከእደጥበብ ውጠቶች ውስጥ ተፈጥሯዊ ግብዓቶችን ብቻ በመጠቀም ይሚሰሩትን እንደ ሸመና፣ የሸክላ ስራዎች፣ የሠፌድ ስራዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ የቅርጫት ስራዎች ይገኙበታል፡፡ በሀገራችን የሚገኙትን ጌጣ ጌጦች ስንመለከት እንደሚገኙበት ማህበረሰብ እና አካባቢ ያላቸውም ትርጉም እና ጌጣጌጦቹ የሚደረጉባቸው የዕድሜ ክልል የተለያየ ነው፡፡ እነዚህ የጌጣ ጌጥ ስራዎችን ለመስራት እንደ ወርቅ፣ ብር፣ ነሃስ፣ ጨሌ፣ ዛጎል እንዲሁም የተለያዩ ብረታብረቶችን ይጠቀማሉ፡፡

የመማር ማስተማሪያ ስልት፦

- ገለፃ ማድረግ
- የተለያዩ ባህላዊ የዕይታ ጥበባት በስዕል፣ በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ማሳየት
- ያዩትን የዕይታ ጥበባት በስዕል እንዲሰሩ ማድረግ

የመማር ማስተማሪያ መሳሪያ

- ጥቁር ወይም ነጭ ሰሌዳ
- ጠመኔ ወይም የነጭ ሰሌዳ መፃፍያ
- እርሳስ
- ከለር

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የኢትዮጵያን ሙዚቃ የምናደንቅባቸውን ጥቂት ምክንያቶችን ተቀምጠዋል፡፡ በተጨማሪም የሃገራችን ባህላዊ መሳሪያዎችን እንደዚሁ በጥቂቱ አይተናል፡፡ የሃገራችን ሙዚቃ የሚለይበትንም ትንሽ ምክንያት አይተናል፡፡ የተቀመጡትንም መዝሙራት ብንለማመዳቸው ቅኝቶችን ከማስገንዘብ በላይ ሃገራዊ ፍቅርና አንድነትን ስለሚረዱበት በደንብ ማስረዳት ተገቢ ነው፡፡

በሀገራችን ብዙ የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ይገኛሉ፡፡ ከአራተኛው እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን የተሰሩትን የዕይታ ጥበባት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ በቀደመው ጊዜ በሃገራችን ሲሰሩ የነበሩት የቀለም ቅብ ስራዎች በአብዛኛው በአብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም አቢያተ መንግስታት አካባቢ ይሰራሉ፡፡ በኢትዮጵያ የነበሩት የኪነ ህንፃ ጥበባት ታሪካዊ ይዘት ያላቸው እና ወጥ ድንጋይን በመፈልፈል እንዲሁም ዲንጋዮችን ጠርቦ በመደርደር ይሰሩ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄረሰቦች የሚያጌጡባቸው ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች የራሳቸው መገለጫ ያላቸው እንዲሁም በተለያየ የዕድሜ እርከን የሚደረጉ ናቸው፡፡

ማጠቃለያ ምዘና

<u>የሚከተሉትን ጠያቂዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ፡፡</u>

1. ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሀገር ዜጎች ሙዚቃቸውን በመስማት ብቻ መለየት ይችላሉ፡፡ <u>እውነት</u>
2. ሙዚቃ ከኢትዮጵያውያን ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ <u>እውነት</u>
3. ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሉም፡፡<u>ሐሰት</u>
4. ሙዚቃን ለበርካታ አላማ እናዜመዋለን፡፡<u>እውነት</u>
5. በነጭ ቅኝ ገዢ በመገዛታችን ሙዚቃችን የውጭ ተጽዕኖ አለበት፡፡<u>ሐሰት</u>
6. በሀገራችን ከሚሰሩ የዕይታ ጥበባት ውስጥ ሰፊውን ስፍራ የሚይዘው ጌጣ ጌጦች ናቸው፡፡ <u>ሀሰት</u>
7. በኢትዮጵያ የሚገኙት ታሪካዊ ኪነ ሕንፃዎች ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍለው ብቻ ነው የተሰሩት፡፡ <u>ሀሰት</u>
8. በሀገራች ያሉ የቀለም ቀደምት ቅብ ስራዎች ሀይማኖት ላይ ያተኩሩ ነበር፡፡ <u>እውነት</u>
9. ባህላዊ ጌጣጌጦች ከወርቅ፣ ብር ፣ ጨሌ ፣ ዛጎል የመሳሰሉትን በመጠቀም ይሰራሉ፡፡ <u>እውቀት</u>
10. ታሪካዊ ቀለም ቅብ ስራዎችን ለመስራት የተለያዩ የፋብሪካ ኬሚካሎችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ <u>ሀሰት</u>

# ምዕራፍ አምስት

## ጥመርታ ዝምድናና፣ ትግበራ

### የቡድን ስራ

የክወናና የዕይታ ጥበባት ብቻውን የሚቆም ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ትምህርቶች ጋር ከፍተኛ ቁርኝትና ትስስር ያለው በመሆኑ ይሄንን ዝምድና በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በትያትር እና በእይታ ጥበባት ያለውን ተዛምዶ እንመለከታለን፡፡ ይህንንም ትስስር በዜማ በውዝዋዜ በድራማና ጭውውት እንዲሁም በስነ ስዕል ጥበብ በማዋሃድ እንረዳለን፡፡

**አጠቃላይ አላማ:-**

- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ያቀርባሉ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በሚና ጨዋታ ያቀርባሉ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በውዝዋዜ ያቀርባሉ፡፡
- የአገራዊ ጥበባትን (በኢትዮጵያ የሚገኙትን የክወናና የእይታ ጥበባትን) በዝማሬ፣ በውዝዋዜ፣ በሚና ጨዋታ፣ በሥዕልና በፍቶግራፍ የተሰሩት ስራዎችን ያደንቃሉ፡ ፡

### 5.1 የቡድን ስራ ከሙዚቃ አንፃር

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ:-**

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ:-

- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ዝምድና ይረዳሉ
- በሚያውቁትን መዝሙር መልእክቱንና ዝምድናውን ይገልፀሉ

የቡድን ስራ በብዙ የሙያ መስኮች ላይ ያለ ቢሆንም፤ ሙዚቃ ግን በተለይ የቡድን ስራ ያለው ሙያ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ዜማ ቢደርስ፡ ግጥም፣ ቅንብር፣ ሙዚቃ መሳሪያን መጫወት፣ ድምፃዊ፣ ድምፅ ማስተካከል፣ ማተም፣ ማሰራጨት፣ ሽያጭ …ወዘተ በሌሎች ሰዎች የሚሸፈኑ ሙያዎችና ስራዎች ናቸው፡፡

አንድ ሰው ብቻውን ወይም ከሌሎች ጋር በአንድነት ሙዚቃን ሊጫወት ይችላል፡፡ በግል ክህሎትን ለማዳበር መለማመድ ተገቢ ቢሆንም ከሌሎች ጋር አብሮ መስራት የራስን ችሎታ ከማሳደግ ባለፈ ያለንን እውቀት ለሌሎች እንድናስተላልፍ ያስችለናል፡፡ በቡድን መስራት ከአንድ ግለሰብ ባለፈ ለሌሎችም እንድናስብ ስለሚያደርገን የማህበራዊ ኑሮ ክህሎታችንን እናዳብርበታለን፡፡

### 5.1.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር

ሙዚቃ በባህሪው የማነቃቃትና ማዝናናት ባህሪ ስላለው ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም በዜማ ማዋሃድ  ጥሩ ውጤት ያስገኛል፡፡

### 5.1.2 የሙዚቃ ኖታ የሂሳብ ስሌትን ጋር፡- የሙዚቃ ኖታ የሂሳብ ስሌትን የሚጠቀም በመሆኑ የሂሳብ ትምህርት ባህሪያትን በሙዚቃ ውስጥ እናገኘዋል፡፡

ምሳሌ፡-

- ✓ አራት ሩብ ኖታ እኩል ይሆናል አንድ ሙሉ ኖታ፡፡ (የመደመር ባህሪ)
- ✓ ግማሽ ኖታ እኩል ይሆናል ሁለት ሩብ ኖታ፡፡ (የማካፈል ባህሪ)
- ✓ ሙሉ ኖታ እኩል ይሆናል ሙሉ ኖታ እረፍት፡፡ (አቻ እኩልነት ባህሪ)
- ✓ ሌሎቹንም የተማሩትን ከሂሳብ ትምህርት ጋር በማቆራኘት ማስረዳት ይቻላል፡፡

#### መልመጃ 1፡-

1. አንድ ሩብ ኖታ አቻ እረፍት ኖታ ምንድን ነው? <u>እሩብ እረፍት</u>
2. ሁለት ግማሽ ኖታ ስንት ሩብ ኖታ ይሰጠናል? <u>ሁለት</u>
3. አንድ ሙሉ ኖታ ስንት ግማሽ ኖታ ይወጣዋል? <u>ሁለት</u>

### 1.1.3 የሙዚቃ ትምህርት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር፡- የሙዚቃ ትምህርት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር  ከፍተኛ ቁርኝት አለው፡፡

- ✓ ድምፅ በእርግብግቦሽ የሚፈጠር ነው፡፡ ይህንንም የሚያጠናው ሳይንስ ነው፡፡ የተፈጥሮ ሳይንስ ስለድምፅ በምን መልኩ እንደሚፈጠር የርግግቦሹን መጠን አጥንቶ እያንዳንዱ ድምፅን በቁጥር አስቀምጧል፡፡
- ✓ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዋነኝነት ከተፈጥሮ ውጤቶች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከተለያዩ አይነት እንጨት፣ ቆዳ፣ ቀንድ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ከሳይንስ ውጤት ከሆን ነገሮች ሊሰሩ (ፕላስቲክ፣ ማይካ፣ አለሙኒየም፣ መዳብ፣ ላስቲኮች፣ ጎማዎች…ወዘተ) ይችላሉ፡፡

- ✓ ድምፅ ተፈጠሯዊ በመሆኑ የሙዚቃ ድምፃችም እንዲሁ የተፈጥሮ ውጤት ናቸው፡፡
- ✓ አካባቢያችንን ራሱ ዜማ አለው፡፡ (ወንዞች፣ ጫካ፣ የወፎች ዝማሬ፣ እንስሳት ድምፅ፣ የሰዎች ሁካታ ወዘተ፡፡ በጥልቀት ካደመጥነው መሳጭ ድምጾች ናቸው፡፡

መልመጃ 2፡-

1. የሙዚቃ መሳሪያ በአካባቢያችን በምን በምን ሊሰራ ይችላል? መልስ፡- ከእንጨት፣ ከቆዳ፣ ከቀንድ፣ ሸንበቆ፣ ፕላስቲቸ፣ ማይካ፣ አለሙኒየም…ወዘተ
2. በአካባቢያቸው የሚያውቁትን የእንስሳትን ወይም የተፈጥሮ ድምፅን ያስመስሉ፡፡ መልስ፡- የእንስሳት፣ የሰዎችን፣ የወንዝ (ፏፏቴ)፣ የማሽን …ወዘተ

ሙዚቃ ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር፡- ሙዚቃ ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር ዝምድና አለው፡፡

- ✓ ሙዚቃ ዜማ በውስጡ ግጥሞችንና ቃላቶችን የያዘ በመሆኑ ቋንቋ ላይ ያለንን ግንዛቤና እውቀት ያዳብርልናል፡፡
- ✓ ሙዚቃን በመስማት የማዳመጥ ችሎታን፣ በመዘመር የመናገር ችሎታን፣ ዜማና ግጥም በመፃፍ የመጻፍና የማስተዋል ችሎታን እናዳብርበታለን፡፡
- ✓ ሙዚቃ መስማትና መጫወት ንቁ ዜጋ ያደርጋል፡፡
- ✓ ሁል ጊዜ በመጀመሪያው ተማሪዎች እንዲነቃቁና እውቀትን በቶሎ እንዲቀበሉ ሙዚቃ ያዘፍኗቸው፡፡

### 1.1.4 ሙዚቃ ከኤሌክትሮኒክስ ጋር፡- ሙዚቃ ከኤሌክትሮኒክስ ጋር ከፍተኛ ዝምድና አለው፡፡

የሙዚቃ ማጫወቻዎች፣ የሙዚቃ ድምፅ ማጉያዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጭምር የኤሌክትሮኒክስ ውጤት ናቸው፡፡ በመሆኑም ለቴክኖሎጂ የሚኖረንን ግንዛቤ እናሳድግበታለን፡፡

- ✓ ቴክኖሎጂ መጠቀም እንድንችል ያስችለናል፡፡

ለምሳሌ በሞባይላችን ሙዚቃ መክፈት፣ ድምፅ መጨመርና መቀነስ፣ የድምፅ ማመጣጠኛውን (equalizer) ማስተካከል፣ ሙዚቃ በምንፈልገው ቦታ (folder) ማስቀመጥ፣ ሙዚቃን መቁረጥ (ማሳጠር)፣ መሰረዝ (delete)፣ ለሌሎች ማጋራት፣ ከሌሎች መቀበል….ወዘተ ቴክኖሎጂን ሙዚቃ ላይ መገልገላችንን ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

### 1.1.5 ሙዚቃ ለእርስ በራስ ግንኙነት፡- የአንድን ትምህርት ቤት ተማሪዎች እርስ በራስ የሚኖራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ከመምህራኖቻቸውና ከአስተዳደሩ ጋር ተግባቦታቸውን ያሻሽላል፡፡ በዚህም ጥሩ መማር ማስተማር ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

- ✓ መምህር የተማሪዎችን ፍላጎት በመጠየቅና በመረዳት የሚወዱትንና የሚያዝናናቸውን ሙዚቃ ከትምህርት ክፍሉ በፊትና ቀድመው እንዲያዜሙ ያድርጉ፡፡ ይህ በሁሉም ትምህርት መምህራን ቢሆን ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

መልምጃ 3:-

1. ተማሪዎች በቤታቸው ከሰሙት ማንኛውም አይነት ሙዚቃ የተወሰነውን ግጥሙን ፅፈው ያሳዩ፡፡
2. ተማሪዎች በቤታቸው የሚያዳምጡትን ሙዚቃ (ዜማ) ድምፁን በማስመሰል ይለማመዱ፡፡
3. በሚያውቁት ዜማ የራሳቸውን አዲስ ግጥም በማስገባት ለመምህራቸው ያሳዩ፡፡

### 1.1.6 ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር:- ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው፡፡

- ✓ ታሪክ ነጋሪ ሙዚቃ ቀደም ሲል የነበሩት ሰዎች ያደረጓቸውን ድርጊት፣ ሁኔታ የሚገልፅ ግጥም ያለው ሙዚቃ ማለት ነው፡፡
- ✓ ታሪክ በሙዚቃ ተቀምሮ ሊቀመጥና ከትውልድ ወደትውልድ ሊሸጋገር ይችላል፡፡
- ✓ ሙዚቃም የራሱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው መሆኑ
- ✓ ታሪክ በሙዚቃ ሲነገር በቀላሉ የማይረሳ፣ ስሜትን ቀስቃሽ መሆኑ ...ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡

መልመጃ 4:-

1. ከምታውቁት ታሪክ ነጋሪ ሙዚቃ አንዱን ለመምህራችሁ መርጣችሁ ዘምሩ፡፡

2. ተማሪዎች ለክፍላችሁ ይሆናል የምትሉትን አንድ ዜማ ሁላችሁም በመስማማት ትመርጡና ለክፍላችሁ መለያ ይሆናችሁ ዘንድ በቀን በቀን በጋራ ዘምሩት፡
፡ የመረጣችሁትን ዜማ ለክፍላችሁ እንደ አርማ (መለያ) እንዲሆናችሁ በስፖርታዊ ውድድርና በሌሎችም ክፍላችሁ በሚኖረው ተሳትፎ በጋራ ዘምሩት፡፡

የመልመጃ መዝሙር ርዕስ:- ልምምድ
ቀጥሎ የቀረቡትን መነሻ ዜማዎች ቀድመው እረስዎ በመለማመድ በቀጣይ ተማሪዎቹን አለማምዷቸው፡፡



<u>ልምምድ</u>

መዚቃ የሚወድ ያጨብጭብ ቸብቸብ፤

መዚቃ የሚወድ ያጨብጭብ ቸብቸብ፡፡

መዚቃ የሚወድ ይደንስ  ዳንስ ዳንስ፤

መዚቃ የሚወድ ይደንስ  ዳንስ ዳንስ፡፡

ሂሳብን የሚወድ ይደምር ቸብቸብ፤

ሂሳብን የሚወድ ይቀንስ ቸብቸብ፡፡

ሂሳብን የሚወድ ያባዛ ቸብቸብ፤

ሂሳብን የሚወድ ያካፍል ቸብቸብ፡፡

ቋንቋንም የሚወድ ያዳምጥ ቸብቸብ፤

ቋንቋንም የሚወድ ይናገር ቸብቸብ፡፡

ቋንቋንም የሚወድ ያንብብ ቸብቸብ፤

ቋንቋንም የሚወድ ይፃፍ ቸብቸብ፡፡

የመልመጃ የመዝሙር ርዕስ ፡- እንነሳ በጥዋት

ቀጣዩን መዝሙር ቀድመው መምህር ይለማመዱትና ለተማሪዎችዎ ያለማምዷቸው፡፡



ዶሮ ጮኸ በጥዋቱ፤

እንነሳ እንሁን ብርቱ።

ያልነቃ ሰው ጠዋት ቀድሞ፤

ብርቱ አይሆንም ፈፅሞ።

እንነሳ በማለዳ፤

ልብስ እንልበስ ጥርስ እናፅዳ።

እንዘጋጅ በደስታ፤

ለስንፍና አንስጥ ቦታ።

መልመጃ 5፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ

1. ከላይ የቀረበው መዝሙር ስለምን እነደሚናገር ይግለፁ።
2. ከዚህ መዝሙር ምን ትምህርት እንዳገኙበት ይግለፁ።

አጠቃላይ የመማር ማስማር ስልቶች

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- በፅሁፍ ማስረዳት
- ማለማመድ
- በግልና በቡድን ማለማመድ
- የተቀዱ ሙዚቃዎችን ማሰማት (ቪዲዮ)
- የቤትና የክፍል ስራ መስጠት
- በትንሽ በትንሹ እንዲለማመዱ ማድረግ።

የመማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ጥቁር ሰሌዳ (ነጭ ሰሌዳ)
- መፃፊያ ጠመኔ (ነጭ ሰሌዳ መፃፊያ)
- ቴፕ (ቪዲዮ) ማጫወቻ
- ኪቦርድ

## 5.2 ውዝዋዜ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

### የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

ውዝዋዜዎችን ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዲረዱ ማድረግ፡፡

- በሚና ጨዋታ ከእፀዋት ውዝዋዜን እንዲቀዱ ማድረግ፡፡
- የተለያዩ አይነት የእንቅስቃሴ ምንጮችን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

ውዝዋዜ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በተለይም ከ ሰውነት ማጎልበሻ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ጋር በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ለትምህርቶቹ ተማሪዎች ለሚኖራቸው አቀባበል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡

ውዝዋዜ ክዋኔ ጥበብ እንደመሆኑ የአካል እንቅስቃሴን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው፡፡ ለዚህም ውዝዋዜ በምናደርግበት ጊዜ ሙሉ ሰውነታችን ስለሚንቀሳቀስ ከውዝዋዜው ባለፈ ጤነኛ የሆነ የሰውነት አቋም እና የአተነፋፈስ ስርአት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ይሄ ደግሞ ለማንኛውም የትምህርት ዘርፍ የሚያገለግል መሰረታዊ የሆነ የጤና ስርዓት ነው፡፡

- ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን እንቅስቃሴ ደረጃ በደረጃ በመስራት እንዲሰሩ ማድረግ፡- እነዚህ መደበኛ ያልሆኑና ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎች ሲሰሩ በተቃራኒው ሊኖራቸው ስለሚገባ ስለመደበኛና ቀላል የእርምጃ እንቅስቃሴ ምንነት ግንዛቤ ያዳብራሉ፡፡

### የመለማመጃ ቅደም ተከተል፡-

- ከታች የተቀመጡትን ትዕዛዛት በአግባቡ እንዲተገብሩት ማድረግ፡፡
- እያንዳዱን እንቅስቃሴ ለሶስት ሶስት ደቂቃ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ሂደቱን መከታተል፡፡
- ጉልበት ሳይታጠፍ እጆች ቁልቁል ተንጠልጥለው ላለመንቀሳቀስ ድርቅ እንዳሉ፡ አንገት ቀጥ እንዳለ፡ ወገብም እንዲሁ እንደተገተረ ውጥረት በነገሰበት አይነት እርምጃ አካሄድ በክፍል ውስጥ እንዲቀሳቀሱ ማድረግ፡፡
- የሰውነት ክብደታችንን ሙሉ በሙሉ ተረከዞቻችን ላይ በማሳረፍና መላው ሰውነታችንን ፍጹም ላላ ዘና በማድረግ ለመሬት ስበት ፍጹም ታዛዥ እንዲሆን በማድረግ በዝግታ በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡
- የሰውነት ክብደታችንን ሙሉ በሙሉ በፊተኛው የእግራችን መዳፍ ጣቶች ላይ በማሳረፍ አይኖቻችን በሩቁ አንድ ቦታ ብቻ እንዲያዩ በማድረግ በረጃጅም እርምጃ በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡

- ከዚህ በላይ የቀረበውን የእጸዋት ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ አብቦ እስከ መክሰም ያለውን ሂደት በመከተብ በውዝዋዜ በማቀናጀት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

የመማር ማስተማር ስልቶች፡-

  - የተክሎችን የእድገት ሂደት ከተክል ጀምሮ በቪድዮ ማጫዎቻ እንዲመለከቱ ማድረግ፡፡
  - ሰውነታቸውን ዘና አድርገው ከስር ጀምሮ ያለውን ሂደት እንዲሰሩ ማገዝ፡፡
- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- የምስል ማጫወቻ፣
- መለማመጃ ክፍል
- የምስልና የድምፅ ግብአት

## 5.3 የትያትር ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

የክዋኔ ጥበብ በተለያየ መንገድ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት አለው፡፡ ለምሳሌ ከሳይንስ ትምህርት ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ሲሆን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ከአማርኛ ትምህርት ጋር የንባብ ባህልን ከማዳበር እና ስለ ኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍ እና ትያትር ለመገንዘብ በአያሌው ይጠቅማል፡፡ ለተማሪዎች የክዋኔ ጥበባትን በሚማሩበት ወቅት በራስ መተማመን ያዳብራሉ ፈጣሪ እና ችግር ፈቺ ትውልድ እንዲኖረን የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ዝርዝር አጥጋቢ የማስተማር ውጤት

ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- በሚና ጨዋታ ከዋኔን ከሳይንስ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ይረዳሉ፡፡
- ድራማዎችን ይሰራሉ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት የክቡር ከበደ ሚካኤልን ስንኞች በማንበብ በክፍል ተማሪዎች ፊት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

የማስተማር ስልቶች ፡- ተማሪዎች ይህንን ስንኝ በድራማ መልክ በሚያቀርቡበት ጊዜ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ዝምድና እንዲናገሩ ማድረግ፡፡

## 5.4 የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ስናጣምር ትምህርቶቹን ቀላልና አዝናኝ በሆነ መንገድ እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ ትምህርቱም በንቃት እንዲከታተሉ እና እንዲረዱ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም ፈጠራ የተሞላበት የችግር አፈታት በላቀ ደረጃ እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፡፡ የዕይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር መጣመር በትምህርት ውጤት ላይም ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ያመጣል፡፡

**ዝርዝር የትምህርት ውጤት**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር ያለውን ጠቀሜታ ይረዳሉ፡፡
- ከዋክብትን፣ ወንዞችን ፣ አዕዋፋትን ይመሳሰሉትን የተፈጥሮ አካላት በስዕል ያሳያሉ፡፡
- የሳይንስ ትምህርት በዕይታ ጥበብ ዕይን መመልከት

### 5.5.1 የዕይታ ጥበባት ከሳይንስ አንፃር

የዕይታ ጥበባት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ እንደሚታወቀው በአካባቢያችን እጅግ ብዙ ዓይነት ቀለማት ፣ ቅርፆች ፣ ፎርሞች ያላቸው ተፈጥሯዊ እንዲሁም ሰው ሰራሽ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ከነዚህ በአካባቢያችን ከምናያቸው ተፈጥሯዊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ከዋክብት፣ ልዩ ልዩ ወንዞች፣ አዕዋፋት፣ ተክሎች የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተፈጥሯዊ የሆኑትን ነገሮች ከዕይታ ጥበብ አንፃር በምናይበት ወቅት ስለ ባህሪያቸው ፣ ስላላቸው ገፅታ እንዲሁም ከአካባቢያችን ጋር ያላቸው መዛመድ ቀላል በሆነ መልኩ መረዳት እንችላለን፡፡ ይህም የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችን ላይ ነገሮችን አዲስ እና አስደሳች በሆነ መንገድ እንድንረዳቸው ያስችለናል፡፡

እንደምሳሌ ብንወስድ አዕዋፋትን የዕይታ ጥበባትን ከሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ጋር አጣምረን በምንሰራበት ወቅት የአዕዋፋቱን ዝርያ በቀለማቸው ፣ በፎርማቸው እንዲሁም በላያቸው ላይ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ቅርፆች ያላቸውን ቀለማት መነሻ በማድረግ በቀላሉ መለየት ያስችለናል።

በሌላ በኩል ከዋክብትን በስዕል ስራ ለመስራት በምንሞክርበት ወቅት የምንስራቸውን የከዋክብት ዓይነቶች ፣ መገኛቸውን ብሎም በስርዓተ ህዋ ውስጥ ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳላቸው ለማወቅ እድል ይኖረናል።

ወንዞችን፣ ተራሮችን ፣ እንስሳትን በስዕል በምንሰራበት ወቅት ከአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አንፃር በትምህርቱ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እየሰራን እንደመሆናችን መጠን አካባቢያችንን ለማጤን ፣ ለማወቅ እንዲሁም አካባቢያችንን ከሌላው ጊዜ በተለየ ትኩረት እንድናስተውል ያስችለናል። ይህም ትምህርቱን ከንባብ በተጨማሪ በተግባር እያየን እና እየሰራን ስለሆነ እንዳንረሳው ይረዳናል።

የመማር ማስተማር ስልቶች፡-

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- ደጋግመው እንዲለማመዱ ማድረግ

የመማር ማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-

- ምስል፣
- ምስል ማሳያ መሳሪያ፣
- እርሳስ ፣
- ጭቃ ከለር

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ መሰረታዊ የሆኑትን የሙዚቃ መፃፊያ ኖታ ምልክቶችን ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ፣ ሩብ ኖታ እንዲሁም ሙሉ ኖታ እረፍት፣ ግማሽ ኖታ እረፍት፣ ሩብ ኖታ እረፍት ምልክቶችን አፃፃፍ ከነውክልና ጊዜ ዋጋቸው ለይተዋል። በተጨማሪም እነዚህን ምልክቶች አቆጣጠራቸውን ተለማምደዋል።

እንዲሁም የተለያዩ መልመጃ የሚሆኑ ዜማዎችንና መዝሙሮችን ተለማምደዋል። በመሆኑም በዚህ በሦስተኛ ክፍል የተጀመሩትን የሙዚቃ እውቀቶች እንዳይረሱ በግላቸው ደጋግው በእረፍት ጊዜያቸው መለማመድ ያስፈልጋል። ሙዚቃና ሌሎች የጥበብ ክህሎቶች የግል ፍላጎትንና ጥረትን የሚፈልጉ በመሆኑ ሁልጊዜ በግላቸው ለማወቅና ለመለወጥ ጥረት አንዲያደርጉ ይርዷቸው።

የዕይታ ጥበባት እና የአካባቢ ሳይንስ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማጣመር ትምህርቶቹን ቀላልና አዝናኝ በሆነ መንገድ መረዳት እንድንችል ያደርጋል። በአካባቢያችን የምናያቸውን ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮችን በዕይታ ጥበብ አማካኝነት ማጥናት እና ማበልጸግ አስፈላጊ ነው። አካባቢያችንን እንድናስተውል እንድንጠብቅ እና ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር እነዚህ ጥበባት ይረዱናል

**የማጠቃለያ ምዘና መልስ**

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሐሰት

## ዋቢ መፃህፍት


1. ታሪክና ምሳሌ፣ ክቡር ደ/ር ከበደ ሚካኤል (1999 እ.ኢ.አ)
2. የኢትዮጵያ ታሪክ 1847-1983፤ ባህሩ ዘወዴ (1999 እ.ኢ.አ)
3. Ezra Abate, (2009) Ethiopian kinit (scales), Analysis of the formation and structure of the Ethiopian scale system
4. Ashenafi kebede ,( 1971) The music of Ethiopia ;its development and cultural setting
5. Ellinger, J. (2014) Music theory fundamentals
6. Jones, Russel and Cathrine ( 2021) , understanding basic music theory
7. Bahru Zwede ,(2002) The history of modern Ethiopia 1855- 1991
8. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ 1889-1983 ተስፋዬ ለማ (2005 እ.ኢ.አ)
9. The little book of music theory, Amsco Publications, New York.
10. Harmony 1, Barrie Nettles, Berklee collage of music, (1987)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የ3ኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት
# (Performing and Visual Arts Syllubus for Grade3)

ግንቦት 2013
ቢሾፍቱ

## የሦስተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ይችላሉ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ምልክታቸው ይለያሉ።
- መሠረታዊ ቀለማትን ይለያሉ
- ቀላል የፎቶግራፍ ዘዴዎችን ይለያሉ።
- ቀላል የድራማ አሰራር ዘዴን ይለያሉ።
- በድምፅና በምስል የሚያዩዋቸውንና የሚሰሟቸውን መልክዕክቶችን ምስሎችንና ድርጊቶችን ይለያሉ።
- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው በቀላል የምት መሳሪያዎች ተጫውተው ያሳያሉ።
- የቤተሰባዊ ሚናዎችን በመዝሙር፣ በውዝዋዜ በሚና ጨዋታ በማስመሰል ያሳያሉ።
- ሥዕሎችን ስሎ ማሳየት፣ ቀለማትን መደባለቅ ማተምና መቀባት።
- ብዝሃነት ላይ ያተኮረ ያለፈውንና የአሁኑን የዕይታ ጥበባትን ያወዳድራሉ።
- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ያቀርባሉ፤
- የአካባቢውን ጥበብ በሚና ጨዋታ ያቀርባሉ፤
- የአካባቢውን ጥበብ በውዝዋዜ ያቀርባሉ፤
- የጎበኟቸውን ባህላዊ ቦታዎች ሪፖርት በቃል ያቀርባሉ።
- የአገራዊ ጥባትን (በኢትዮጵያ የሚገኙትን የክወናና የእይታ ጥበባትን) በዝማሬ፣ በውዝዋዜ፣ በሚና ጨዋታ፣ በሥዕልና በፎቶግራፍ የተሰሩት ስራዎችን ያደንቃሉ።

## የሦስተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት

| **የጭብጥ መስክ** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶች** | **መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|---|
| **ጥበባዊ ግንዛቤ**<br>29 ክ/ግዜ | ክፍል 1:<br>1. መለየትና ማስረዳት -<br>1.1. ከሙሉ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ እስከ ሩብ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ<br>1.2. መሠረታዊ ቀለማት<br>**1.3. ቀላል የፎቶግራፍና** | • ተማሪዎች ከሙሉ የድምፅና የእረፍት ኖታ እስከ ሩብ የድምፅና የእረፍት ኖታ ድረስ እንዲለማመዱ ይደረጋል።<br>• በተሰጣቸው የድምፅና ቪዲዮ መሰረት መልዕቶችን፡ ምስሎችንና ድርጊቶችን እንዲለዩ ይደረጋል።<br>• መሠረታዊ ቀለማትን ይለያሉ። | • የመለማመጃ ክፍሎች፡<br>• ምስሎች<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ |

| የሣስተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የጭብጥ መስክ** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶች** | **መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች** | **ምዘና** |
| | | እንዲለማመዱ ይደረጋል። | መስሚያ ግብዓቶች፤<br>• እርሳስ፣ ጭቃ ከሰርና በከባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | |
| **ጥመርታ ህምድናና፣ ትግበራ** | **ክፍል 5**<br>**5.የቡድን ስራ**<br>5.1. ክ.ዕ.ጥን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር | • በግሩፕ ዝማሬ፣ በውዝዋዜ በሚና ጨዋታ ተፈጥሮን ለመግለፅ እንዲበረታቱ ይደረጋል።<br>• ተማሪዎች ስለተፈጥሮ (ስለከዋክብት፣ ስለወንዝ፣ ስለአዕዋፋት ወዘተ.) እንዲዘምሩ ይደረጋል። | • የመለማመጃ ክፍል፣<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤<br>• የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፤<br>• ምስሎች፤<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤<br>• እርሳስ፣ ጭቃ ከሰርና በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ<br>• ግለግምገማ<br>• የቃል ጥያቄ |

# የክወናና የዕይታ

# ጥበባት ትምህርት

## 3ኛ ክፍል

2014 ዓም/2021

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ